# “እንደሠራ አይገድል” - ዘርፌንና እዩ ጩፋ ሲተቃቀፉ ደግሞ አየሁ....

ይኄይስ አእምሮ

ፖለቲካው ስልችት አለኝና እስኪ ደግሞ ወደ ሃይማኖቱ ጎራ፣ ጎራ ብዬ አንዳንድ ጉድ ልታዘብ አልኩና ጎራሁላችሁ ፡፡ በዩቲዩብ ነው ታዲያ፡፡ ከዚያ በፊት ግን የነአበበ ገላውን አቀባበል ተመለከትኩና በጣም ከመደሰቴም በተጨማሪ በሀገራችን የመጣው የለውጥ ንፋስ ተስፋ ሰጭ እንደሆነ ጠረጠርኩ፡፡ በተለይ አበበ ገላው ከገባ በውነት ትልቅ ለውጥ አለ ማለት ነው፡፡

ብዙ ምስል ከሳች አባባሎች አሉን፡፡ በርዕሴ የተመለከተው “እንደሠራ አይገድል”ን የሚስተካከል ግን የሚኖር አይመስለኝም፡፡ እኔ ራሴን የዛሬ 30 ዓመት ገደማ ብታዩኝ - በስማም! - (የመልኬን ነገር ለጊዜው እርሱትና) ንግግሬና ጥርስ አይከድንነቴም ሆነ የአለባበስ ሽቅርቅርነቴ ልዩ ነበር - ልክ እንደያኔው ፍቅረ ሥላሤ ወግደረስ፡፡ ዛሬ ግን የተጣመመ የጉሊት ጣሳ መስዬ ብናገር ሰሚ የለ፤ ብቀልድ ለመሣቅ የሚተባበረኝ የለ - ታዲያንስ “ሲያልቅ አያምር፤ “‹እንደሠራ›ም አይገድል” ማለት እንደዚህ አይደል? ዓለም እንግዲህ እንዲህ ናት፡፡ የሚረዳት ግን ጥቂት ሰው ብቻ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ መጨረሻዎች እንመጀመሪያዎች አይሆኑም ብቻ ሣይሆን አያምሩም፡፡

ዘርፌ ከበደን በመዝሙሯ አውቃታለሁ፡፡ ቆንጆ ድምፅ አላት፡፡ ነፍስያዋ ግን አሁንም ድረስ ዕረፍት ማግኘት የቻለች አልመሰለኝም፡፡ ከሀሰብ እስከ አዲስ አበባ፣ ከዚያም እስከዐረብ ሀገር ያንከራተተቻትን ሴት አሁንም ድረስ ታቅበዘብዛት ይዛለች፡፡ ከብዙ የሕይወት ውጣ ውረድ በኋላ ባገኘችው የዝማሬ ተሰጥዖ ፈጣሪዋን በኦርዶቶክስ ቅጽረ ግቢ ለተወሰኑ ዓመታት አገለገለች፡፡ በኋላ ደግሞ አንዳች መንፈስ በዚህች ልጅ ቀንቶ ከዚያ አስፈንጥሮ አወጣትና በማጭበርበር ሥራው ወደምናውቀውና እዩ ጩፋ ወደሚባለው የዲያብሎስ አገልጋይ ወሰዳት፡፡ የሚገርም ዝውውር ነው፡፡ እኛ የምናውቀው የዝውውር መስኮት ከአርሴ ወደ ማንቼ ነበር፡፡ እኔ ለምሣሌ በቲፎዞነትም ቢሆን ከሪዲንግ (Reading Football Club) ወደ ቼልሲ (Chelsea) ዞሬ ይሄውና ማታ ማታ ሳላስተጓጉል መቸለሴን ተያይዤዋለሁ፡፡ የቼልሲ ክለብ አባል መሆን ብዙ ነገር ያስረሳል፡፡ ጨዋታው ሲሞቅ የሚሰጥህ ጊዜያዊ ደስታ እንዲህ እንዳይመስልህ፡፡ በተለይ በወር መጀመሪያ ከሆነማ ጨዋታው ቀን ከሌት ቢሆን ደስ ይልሃል፡፡

የሚገርም ዘመን ላይ እንዳለን ልባም ልብ ይበለው፡፡ በመሠረቱ እኔ ራሴም በሃይማኖታዊ ጎራ ብዙም አልጨነቅም፤ አላከርምም፡፡ አክራሪነትን ብዙም አልደግፍም፡፡ “የሚያድነውን መንገድ ፈጣሪ ነው የሚያውቀው” የሚለው ብዙም አይጎረብጠኝም፡፡ ይቺ “የኔ መንገድ ብቻ ናት የምታዋጣው” ዓይነት ቀኖናም አሁን አሁን የምትመቸኝ አልሆነችም፡፡ በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ ሃይማኖቶች በዓለማችን እንዳሉ ተረድቻለሁ፡፡ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ከክርስትና ውጪ ባሉ ሃይማኖቶች ሥር እንደተኮለኮሉ ተገንዝቤያለሁ፡፡ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ምንም ዓይነት ሃይማኖት እንደሌላቸው ወይም የባዕድ እምነት ተገዢዎች እንደሆኑ አንብቤያለሁ፡፡ ሀብታሞችንና የመንግሥታት መሪዎችን በዋናነት ጨምሮ ቁጥራቸው ቀላል ያልሆነ ብዙ የዓለም ዜጎች ኢአማኒና አንቷን ሌቪ የተባለ አሜሪካዊ ካህን በይፋ የመሠረተው የChurch of Satan ተከታይ እንደሆኑ አውቃለሁ፡፡ ስለዚህ ይህን ሁሉ ቢሊዮን ሕዝብ ይህን ወይ ያን ሃይማኖት ባለመከተሉ ብቻ የሚያጸድቅ ወይም የሚኮንን የጋራ አባት አለ ብዬ ማመን ይከብደኛል፡፡ ፈጣሪ አንድ ነው፡፡ ዓለምን የፈጠረ ለእስላሙ ጥቁር ለክርስቲያኑ ቀይ ወይ ነጭ አምላክ የለም፡፡ ችግሩ የአመለካከትና የእምነት ጉዳይ ነው፤ ችግሩ የሰዎች መብዛት ያመጣው በተለያዩ ነገሮች የመለያየት ጣጣ ነው፡፡ (አንዲት ዚቅ ላስታውሳችሁና ከፈለጋችሁ ፈገግ በሉባት - አንድ ሼህና አንድ ቄስ ጓደኛሞች ናቸው፡፡ ሼሁ ለቄሱ “መምሩዋ ተስላምና ታማራ (በቀድሞው ዕውቀት ክርስቲያን ማለታቸው ነው) ማንኛቸው ይጠድቃሉ?” ብለው ይጠይቋቸዋል፡፡ ቄሱም ብልኅና አስተዋይ ነበሩና “አየ ሼህዋ - ተሁለት አንድኛቸው እንታናቸውን መብላታቸው አይቀርም፡፡” አሏቸው ይባላል፡፡ እንደኔ ደግሞ ከሁሉም ጎራ ያለው እንደየሥራው ያገኛታል እንጂ በስም መዳን የለም ወይም ያለ አይመስለኝም፡፡ የራሴ ሃሳብ ነውና ማንንም አይመለከትም፡፡ ልከራከርበትም ለጊዜው ዝግጁ አይደለሁኝም፡፡)

የሆኖ ሆኖ ጽድቅና ኩነኔን በተመለከተ ከሰውኛው መከፋፈል በተቃራኒ በበኩሌ በዐይነ ውኃው አንድን ሰው ማወቅ አያቅተኝም፡፡ ከዚያ ሰው ጋር ለተወሰኑ ደቂቃዎች ከነዚህም ደቂቃዎች ብዙዎቹን እርሱ እያዋራኝ ከቆየሁ ስለዚያ ሰውዬ ውስጣዊ ስብዕና የተወሰነ ነገር ይገባኛል፡፡ ከዚያም በመነሣት ሃይማኖቱ ምንም ይሁን ምን መጥፎና መልካም ስብዕና እንዳለውና እንደሌለው መገመት አይከብደኝም፡፡ በዘመነ ክርስቶስ በእምነታቸው ምክንያት ተከታዮቹና አማኞቹ ያገልሏቸው የነበሩ ሰዎችን ክርስቶስ እየቀረበና እያ(ስ)ቀረበ ስንትና ስንት ተዓምራትን ሠርቶላቸዋል፡፡ ስለዚህ በጌታ ፍጡራን መካከል ጣልቃ እየገቡ “እገሌ ይጸድቃል፤ እገሌ አይጸድቅም” ብሎ በጎራ ሰዎችን መፈረጅ አግባብነት ያለው አይመስለኝም - ከመነሻው፡፡ በሥራቸው እንዳኛቸው ይልቁንስ፡፡ የዘርፌን በሆነ መንፈስ መጠለፍ በግልጽ የምናገረው በዚያ ቦታ በክርስቶስ ኢየሱስ ስም የሚሠራውን -

በልጆች አነጋገር “ፊንታ” ልበለው ይሆን? - ብቻ በዚያ ሥፍራ የሚታየውን ዐይን ያወጣ ማጭበርበርና ዝሙት በደምብ ስለምረዳ ነው፡፡ ፈራጁ አንድዬ ቢሆንም የነፍሴን መመስከር አለብኝ፡፡ ጌታም እኮ “በፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ” ይላል፡፡

ከዚህ አንጻር ዘርፌ ነፍሷ ተጨንቃባት የመረጠችው መንገድ ጉዞዋን እንዳሰነካከለባት መገመት አላቃተኝም - ብሳሳት ደስ ባለኝ፡፡ “ነፍስን እንዴት ማዳን ይቻላል” ለሚለው ጥያቄ በዚህች አጭር ማስታወሻ መዘርዘር ያስቸግራል፡፡ በሃይማኖት ዙሪያ መከራከርም ጉንጭን ማልፋት ነው፡፡ ለግንዛቤያችሁ ያህል ደግሞ ከስንት ጊዜ አንዴ ቢሆንም እኔም ከዚያ ሽፋፋ የአዳም ጠላት ጋር የማወራበት - የጦፈ ውዝግብ ውስጥ የምገባበትም- ጊዜ አለ፡፡ በሰዎች ላይ አድሮ ሲያስቸግር ካለሥራየ እየገባሁ ሰዎችን የምረዳበት አጋጣሚ ስላለኝ ከጨለማው መንግሥት ሥውር ታጣቂዎች ምሥጢር የመካፈል ልምድ አለኝ፡፡ ያን ዓይነቱን ተግባር ደግሞ እምነት ያለው ሁሉ ሊያደርገው የሚችል እንጂ ለጥቂቶች ብቻ የተሰጠ ፀጋ አይደለም፡፡ ዋናው እንዳልኩት “ይሆንልኛል፤ ይደረግልኛል” የሚለው እምነት ነው፡፡ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል መጠቀም የሚያስችል ኃይል በጸሎት መላበስ፡፡ በቃ፡፡ ዱዲ አትከፍልበትም፡፡ አንተም፣ አንቺም ሞክሩት፡፡ “ኃጢያተኛ ነኝና ክርስቶስ አይለመነኝም” ካልክም አይለመንህም፡፡ የነገር መጣመም ካለማመን ይጀምራልና አምነህ ጠይቅ፡፡ በዚህች ምድር ማንም ፍጹም አይደለም፡፡ ይሄ መከረኛ ልብስ እየሸፈነን እንጂ በየቀሚሳችንና በየካባችን፣ በየሱፋችንና በየጥምጥማችን ሥር ብዙ ጉዳጉድ አለ - መጽናኛችን ግን የሰዎች ሦስተኛ ዐይን መታወር ነው፡፡ ፍጹም ከሆንማ በዚህች ቆሻሻ ምድር ዱሮውንስ ምን ልንሠራ እንፈጠራለን? ምድር እኮ የመማሪያ ቦታ ናት፡፡ ለንስሃ ግን እጅህን ስጥ - ለእውነተኛ ንስሃ፡፡  በንስሃ የማይጸዳ ስህተት የለም - ቢያንስ በመርህ ደረጃ፡፡

ከፍ ሲል ለመጠቆም እንደሞከርኩት የመዳኛን መንገድ ከመጥፊያ መንገድ ለመለየት ግን የሰውዬውን አካሄድ ማጤን ብቻ በቂ ነው፡፡ በየ “ቸርቹ” የሚሠራውን የጭቡ ሥራ አይተህ ሃይማኖትህን መክዳት የለብህም፡፡ የራስህን ጠጋግነህ ያዝ፡፡ በሁሉም ቦታ ተስፋ አስቆራጭ ነገር ማየትህ ዘመኑ የፈቀደው ፋሽን ነውና አይግረምህ፡፡ አንተ ግን ለትንሹ እግዚአብሔር ለኅሊናህም ታዛዥ ሁን፡፡ “እገሌ እንዲህ ሠራ” ብለህ እርሱን ተከትለህ አትጥፋ - ያ ሰው የሚከፈለው በሠራው ልክ ነውና የጥፋት ተባባሪ ብትሆን ወይም ተወናብደህ ብልግናን ብትኮርጅ ዋጋህን አታጣም፡፡ የኃጢአት ዋጋ ክፍያ ደግሞ በሰውነት ትልቅነትና ትንሽነት አይለካም፡፡

ከአስገራሚው ፖለቲካችን ጎን ለጎን በሀገራችን የምፅዓትን ቀን መቃረብ የሚጠቁሙ በርካታ ሃይማኖታዊና ርኩስ መንፈሳዊ ክስተቶች አሉ፡፡ ተዘርዝረው አያልቁም፡፡ ከአባባ ታምራት ገለታ ጀምረህ እስከ ማርያም ነኝ ባይዋ እስረኛ ሴት ድረስ ብትሄድ (አሁን ተፈትታ ከሆነ አላውቅም)፣ ከ“ንግሥተ ነገሥታት እህተ ማርያም” ጀምረህ እስከ ጥልቁ መሣፍርት የሌላቸው የጴንጤና ኦርቶዶክስ ሐሣዊ ነቢያትና አጥማቂዎች ብትሄድ ነገሩ ሁሉ ግራ ያጋባል - በሃይማኖትና በፖለቲካው ውስጥ ገብተህ ስትቃኝ ስንትና ስንት ዕብድ አለ መሰለህ፡፡ ለነገሩ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ይህን ዘመን አስቀድሞ በሚገባ ነግሮናልና አንዳንዶቻችን ከመደመም ባለፈ አንደነግጥም፡፡ እንደሚከሰት ቀድሞ በተነገረ ነገር መደናገጥ ዝንጉነት ነው፡፡ ገና ስንትና ስንት ከዚህ በላይ የሚያስደነግጥና በፍርሀት ጥርስን የሚያንገጫግጭ ነገር በግምባር እናያለን፡፡ ወቅቱ ሲደርስ ከሰማይ እሳት የሚያወርዱ እዩ ጩፋዎችን እንታዘባለን፡፡ እነዚህ እነእዩና እነእሥራኤል ዳንሳ የሚባሉ ቀፋላዎች እንኳን ባልተማረ ማይም ሰውነታቸው ከምዕራብ አፍሪካ በሚገዟት የመተት ፓኬጅ ብዙ ተዓምር እየሠሩ ነው - ከነሱን መሰል ማይማን አጫፋሪና ተዋናዮቻቸው ጋር፡፡ ሁሌም የሚገርመኝና ከዚህ ትውልድ ጋር ያለኝን ትስስር እስከጠራጠር ድረስ የሚያሳፍረኝ ጉዳይ  በግልጽ በሚታየው የቁጩ ሥራቸው ያ ሁሉ ሰው በነዚያ “ቸርቾች” ወስጥ ሲጃጃል ማየቴ ነው፡፡ ዘመኑ ነዋ! ትንቢትን ማስቀረት ደግሞ አይቻልም፡፡ አዳሜ  አስቀድሞ በተመቻቸ የሀሰት የመዳን ምስክርነት እየተጭበረበረ ወደነዚያ የጣዖት ቤቶች ይጎርፋል፡፡ ከዚያም ሚስቱንና ገንዘቡን እየተዘረፈ ይመለሳል፡፡ ዘመኑ የጭንቅ በመሆኑ ሰዎች የሚሄዱበትንና የሚሆኑት አጥተዋል፤ ከዚህ ይሠውርህ ወንድሜ፡፡ ከዚህ ይሠውርሽ እህቴ፡፡ Believe me, everything is orchestrated.

እነአጅሬ ሊቃነ ጳጳሣቱ በሚሠሩት የጥፋት ሥራ ቤተ ክርስቲያናችን ብትራቆትም የምትታጠብበትና የምትጸዳበት ጊዜ መምጣቱ አይቀርም፡፡  ሰውን አይተን ግን ገደል ከመግባት እንቆጠብ፡፡ ለነገሩ እኔን ምን አገባኝ? አዳሜ እዚያው ሄደሽ እሳቱ በማይጠፋ ትሉ በማያንቀላፋ ገሃነም ውስጥ ለምትንጨረጨሪው እኔን አሁንና እዚህ ምን ጥልቅ አደረገኝ! ግን ግን ይህች ጦቢያ የምትባል ሀገር የተከፈተባት ዐውደ ግምባር አበዛዙ - በሊቀ መልአኩ!

ለማንኛውም አስተማሪና ገምቢ አስተያየት አድራሻየ -  yiheyisaemro@gmail.com